# ኢትዮጵያችን

*አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (ኢትዮጵያችን) ልሳን*

ኢትዮጵያችን ቅጽ 2 ቁጥር 6 ሰኔ ፲፬ ቀን ፪ ሺህ ፲ ዓ.ም.

## ኢሕአዴግ/ህወሓትና የወቅቱ የፖለቲካ አካሄድ

(ድምጽ ቅጂውን ለማድመጥ እዚህ ይጫኑ https://youtu.be/L_iyxVAgyBQ)

የህወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት ላለፉት 27 ዓመታት በተከተለው የዘር ፖለቲካ ሀገሪቱ ዛሬ ለደረሰችበት የወረደ ደረጃ አድርሷታል። በተለይ ላለፉት ሶስት ዓመታት አገሪቱ በህዝባዊ አመጽ ስትናጥ ከርማ በአገዛዙ ውስጥ የጠ/ሚንስትርነት ለውጥ ተደርጓል። ኢሕአዴግ ህዝባዊ አመጹን እንደለመደው በጦር ኃይልና በግድያ ሊገታው ባለመቻሉ እራሴን ገምግሜ ተለውጫለሁ ለዚህም መገለጫው አዲስ ጠ/ሚኒስትር ሾሜአለሁ ብሎናል። የቀድሞው ጠ/ሚንስትር በአዲስ መተካትንም ለመጀመሪያ ጊዜ የተደረገ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር አድርጎ ለማቅረብ ሞክሯል። የተደረገው የጠ/ሚንስትር ለውጥ በራሱ ኢሕአዴግ ውስጥ በመሆኑ ለብዙሃኑ የኢትዮጵያ ህዝብ ሰላማዊ ሽግግሩም ሆነ ለውጡ ገና ብዙ ይቀረዋል።

ጠ/ሚንስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከኢሕአዴግ የወጡ በመሆናቸውና የመጡበት መንገድ የህዝቡን አመጽ ለማቀዝቀዝ በመሆኑ ህዝባችን ሁኔታውን በአንክሮ እየተከታተለው ነው። ጠ/ሚንስትር ዶር ዐቢይ አሕመድ በመጀመሪያ ህወሓት/ኢሕአዴግ ወዶና ፈቅዶ ያስቀመጣቸው ሳይሆኑ የአልበገሬው የኢትዮጵያ ህዝብ ትግል ውጤት ናቸው። ጠ/ሚንስትር ዶር ዐቢይ አሕመድ መሃላ በፈጸሙበት ቀን ካደረጉት ንግግር ጀምሮ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ሲቀበሉ ባሳዩት ሀገርና ህዝብን የማክበር ጨዋነትና ትህትና የህዝባችንን ስሜት በጅጉ ስበዋል። በንግግራቸውም ኢትዮጵያዊነትን በተደጋጋሚ ከፍ ባለስሜት በመግለጻቸው ህዝቡ ጆሮውን ሰጥቶአቸዋል።

ስልጣኑን ከተረከቡም በኋላ

- በተለያዩ የሀገሪቱ የአስተዳደር ክልሎች በመዘዋወር ከህዝብ ጋር ቁጭ ብለው ለመነጋገርና የህዝቡን ችግር ለማድመጥ ያደረጉት ተግባር የሚያስመሰግን ነው።
- ህወሓት/ኢሕአዴግ በሽብርተኝነት ያሰራቸውን ንጹሃን የፖለቲካ፣ የህሊና እና የሃይማኖት እስረኞችን መፍታታቸው ትግሉ ካነሳቸው ጥያቄዎች አንዱ በመሆኑ መልካም ጅምር ነው። ይሁን እንጂ ዛሬም በሺዎች የሚቆጠሩ የፖለቲካ እስረኞች ያልተፈቱ በመሆናቸው ባስቸኳይ እንዲለቀቁ ይገባል። በባዕድ ሀገር ታስረው የነበሩ ዜጎችን አስፈትቶ ወደ ሀገር የመመለሱ ተግባርም በእውነቱ የዜጎችን ክብር የመገንዘብ አኩሪ ግንዛቤ ነው።
- ከጎረቤት ሀገራት ጋር ሉዓላዊነታችንን ባስጠበቀ መልኩ የተጀመረው የወዳጅነት ግንኙነት ጥሩ ጅማሮ ነው።
- የሕዝባችንን የለት ተለት እንቅስቃሴ ገቶ የነበረው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ መነሳቱ ከሚጠቀሱ መልካም ጅምር አንዱ ነው።

- ህወሓት/ኢሕአዴግ የከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካውን ለማስፈጸም ያደራጀው የመከላከያ፣ የደህንነት እና የጸጥታ መዋቅሮችን የማሻሻሉ ተግባር ተጠናክሮ መቀጠል ይገባዋል። ከዝቅተኛ የኃላፊነት ቦታ እስከ ከፍተኛው የስልጣን እርከን በአብዛኛው የተያዘው በአንድ ጐሳ በመሆኑ የማሻሻያ እርምጃው አንድ ወይም ሁለት ኃላፊዎች በማንሳት ብቻ መቆም የለበትም።
- በጠ/ሚንስትር ዶር ዐቢይ አሕመድ በውጭ ሀገር ላሉ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ወደ ሀገር ገብተው እንዲሰሩ የቀረበው ጥሪ የሚበረታታ ቢሆንም አፈጻጸሙ ከወዲሁ ችግር የታየበት ነው። በተናጥል እየተመረጠ ቀደም ሲል በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ከኢሕአዴግ ጋር የሰሩት ድርጅቶች ላይ ብቻ ማተኩሩ አግባብ አይደለም። ለሀገራዊ መግባባት ሁሉንም ያሳተፈ ጉባኤ የሚያስተባብር ተቋም ተቋቁሞ የእርቅና የመግባባት ጉባኤ ተግባራዊ እንዲሆን ያስፈልጋል።

*"አንድ ሀገር አንድ ሕዝብ ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"* ዶር ዐቢይ አሕመድ የአገዛዙ ጠ/ሚር መሆናቸውን በመንተራስ የህወሓት/ኢሕአዴግን አካሄድ በመገምገም በሀገራችን ወቅታዊ የፖለቲካ ጉዳይ ላይ አቋም መያዝ ማስፈለጉን አምኖንበታል። *"ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"* ይዘን የተነሳነው ዓላማ፣ ራዕይና ተልዕኮ እንደተጠበቀ 27 ዓመት ያለ ተቀናቃኝ የገዛው የህወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ማብቃትና ተፈላጊውን የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት የትግሉን አካሄድ በመመርመር መደረግ ይኖርበታል ያልነው ላይ አቋማችንን ለሕዝባችንና ለሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች እናሳውቃለን።

በቅድሚያ በሀገራችን ኢትዮጵያ የሥርዓት ለውጥ ስንል መመልከት ያለብንን እናስቀምጣለን። ጉዳዩን ለማብራራት "የምንታገለው ለምንድን ነው?" የሚለውን ማስቀደም ይጠይቃል። የ*"ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"* ዋናው ግብ በሀገራችን ኢትዮጵያ የሥርዓት ለውጥ ማምጣት ነው። የሥርዓት ለውጥ ስንል ምን ማለታችን ነው? በአጭሩ፦

- 27 ዓመት ያለምንም ተቀናቃኝ ህወሓትን ማዕከል አድርጎ የገዛው የኢሕአዴግ አገዛዝ ማብቃት ማለታችን ነው።
- ዘርንና ቋንቋን ተገን ያደረገ የግዛት ክፍፍል እንዲያበቃና ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት ይበልጥ እንዲጎለብት ማለታችን ነው።
- የዜግነትንና የግለሰብን ያልተገደበ መብት ቅድሚያ የሰጠ የዴሞክራሲ መብት ያለገደብ ለሁሉም ማለታችን ነው።
- ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በየእሥር ቤቱ የሚንገላቱ የፖለቲካና የኅሊና እስረኞች በሙሉ መለቀቅና ወደፊትም በፖለቲካ አቋሙ ማንም ለእሥርና እንግልት እንዳይዳረግ ማለታችን ነው።
- ሥልጣናቸውን መከታ አድርገው የሕዝብ ደም ያለአግባብ ያፈሰሱ፣ የሀገርና የሕዝብ ንብረት የዘረፉ ሕግ እንዲያያቸው ማመቻቸት ማለታችን ነው።
- በተለያየ ምክንያት በመላው ዓለም በስደት ሕይወታቸውን የሚገፉ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገራቸው የሚመለሱበትን መንገድ ማመቻቸት ማለታችን ነው።
- በእስልምናም ሆነ በክርስትና ሃይማኖት የመንግሥት ጣልቃገብነት እንዲያበቃ መሥራት ማለታችን ነው።
- የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለምንም ተጽዕኖና ማጭበርበር በነፃና በግልጽነት በመረጠው ፓርቲ ይተዳደር ዘንድ ከተቋማት ግንባታ ጀምሮ አስፈላጊውን ጥረት ማድረግ ማለታችን ነው።
- ኢትዮጵያ ሀገራችን ከገባችበት የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበረሰባዊ ቀውስ ለማውጣት በባለሙያዎችና በፖለቲካ ድርጅቶች እንዲሁም በሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች የጋራ

ምክክርና ትብብር የዕቅድና የፖሊሲ ቀረጻ በማድረግ እልባት ለመስጠት መጣር ማለታችን ነው።

- የነዚህና መሰል የሀገራችን ቁልፍ ችግሮች ይፈቱ ዘንድ ቆላልፎ የያዛትን የህወሓት ሕገ-መንግሥት በመቀየር ከኢትዮጵያ ልጆች ለኢትዮጵያ የተረቀቀና በሕዝብ ውይይት የሚጸድቅ አዲስ ሕገ-መንግሥት ተግባራዊ ማድረግ ማለታችን ነው።
- ከሁሉም በላይ ለብዙ ሺህ ዓመታት ተከብሮ የኖረው የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት ሳይሸራረፍ ለመጠበቅና ከትውልድ ትውልድ የምትተላለፍ ዘላለማዊት ኢትዮጵያን እውን ማድረግ ማለታችን ነው።

ከላይ ያስቀመጥናቸው ዋና የምንታገልላቸው ዓላማዎችና የወደፊቷ ኢትዮጵያ ራዕያችን ናቸው። ኢሕአዴግ/ህወሓት በሰላምም ሆነ በጉልበት የያዘውን ሥልጣን በሕዝብ ግፊት ቢለቅ ቀጣይ መንግሥት ለአለፉት 50 ዓመታት እልባት ያላገኙትን የሀገሪቷን ችግሮች ሊፈታ እስከ አልተዘጋጀ ድረስ ትግላችን ይቀጥላል።

አንድ ሥርዓት እየተዳከመ፣ ያለውም አገዛዝ በሕዝብ እየተጠላ ሲመጣ ብቅ የሚሉ ቀና አሳቢዎች ባይጠፉም የጠ/ሚር ዶር ዐቢይና ሌሎች ኢትዮጵያውያን አመጣጥ ከዚህ አንፃር ልንመለከተው እንችላለን። ለአለፉት 27 ዓመት በሀገራችንና በሕዝባችን ህልውና ላይ የተከመረ መቅሰፍት አገዛዝ ውስጥ ተስፋ ሊሰጡ ብቅ ያሉ ኢትዮጵያዊ ወገን አድርገን ልንወስዳቸው ይገባል። በሌላም መልኩ ጭፍን አምባገነንና ዘረኛ በሆነው የህወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ውስጥ ኢትዮጵያዊነትን ቀዳሚ በማድረግ የተነሱበትን የመጨረሻ ግብ ከዳር ለማድረስ የፖለቲካ ድርጅቶች እና የሕዝብ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል እንላለን።

እንደ ወያኔ/ህወሓት ፍላጎት ቢሆን ዛሬ የኦሮሞና አማራ ወገኖች ጦር ተማዘዋል፣ እስላምና ክርስቲያኑ እየተፋጀ ነበር። በጥቅሉ የእርስ በእርስ መተላለቅ ዕጣ ፈንታችን ነበር። ሆኖም ወያኔ/ህወሓት አልሰመረለትም። በዚህ ረገድ ጠ/ሚር ዐቢይም ሆኑ፣ አቶ ለማ መገርሳና መሰል ኢትዮጵያውያን በቅንነት ሊታዩ ይገባል። ይህ አካሄድ ግና አሁንም ዜጎቻችን እየተፈናቀሉ፣ እየታሠሩ፣ እየተገደሉ ቅድሚያ ለሌላ የሚሰጥበት ወቅት ላይ እንዳልሆንን ልናስገነዝብ እንወዳለን። የአማራው በየቦታው መፈናቀልና መሰደድ፣ የኦሮሞዎች አሁንም በየእሥር ቤቱ መታጎርና መማቀቅ፣ እንዲሁም በተለያዩ ጎሳዎች መካከል እየተከሰተ ያለው የእርስ በርስ ግጭት ቀዳሚ የሀገሪቷ ችግር በመሆኑ ጠ/ሚሩ ትኩረት በመስጠት ከሕዝብ ጋር ለመከላከልና ለማስቆም በአንዳንድ አካባቢዎች የጀመሩት ጥረት ቀጣይነትና ክትትል ሊደረግበት ይገባል እንላለን።

የወያኔ/ህወሓት አስኳል አመራሮች እንዲህ ቀላል እንዳይመስሉን። አሥራ ሰባት ዓመት በበረሃ፣ 27 ዓመት በአገዛዝ ተንኮል የተካኑና የሰለጠኑ መሆናቸውን መናቅ የለብንም። አሁንም የሀገሪቷ ቁልፍ የስለላና ሥልጣን እርከኖች በቁጥጥራቸው ሥር ይገኛል። በዚህ ሂደት ውስጥ ብቅ ያሉትን የአቶ ለማ መገርሳ ቡድንና የጠ/ሚር ዶር ዐቢይ አሕመድ አካሄድ ታጋይ የፖለቲካ ድርጅቶች መሠረታዊ ጥያቄዎቻችንን ሳንዘነጋ ልንጠቀምበትና ድጋፍ ልንሰጣቸው ይገባል እንላለን።

"***ኢትዮጵያች ሕዝባዊ ንቅናቄ***" በአለፉት 75 ቀናት በህወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ እየተካሄደ ያሉትን ሁኔታዎች በመመገምገም ከተመለከትናቸው አሉታዊ ጎኖች መካከል፦

- ግንቦት 28 ቀን 2010 ዓ.ም. የኢሕአዴግ ሥራ አስፈጻሚ አካል በጠ/ሚር ዐቢይ ሰብሳቢነት በአደረገው ስብሰባ በሙቶ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን መስዋዕትነት የከፈሉበትን ባድመ፣

ዛላአንበሳና ጾረና ግዛቶቻችንን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለሻቢያ/ኤርትራ አሳልፎ ለመስጠት የተደረሰው ውሳኔ በሀገራችን ኢትዮጵያ ላይ የተቃጣ የህልውና ጉዳይ አድርገን እንወስደዋለን። ውሳኔው ቀደም ሲል በጠ/ሚር መለስ ዜናዊ አመራር የተላለፈ ቢሆንም ይህንን የተሳሳተ የህወሓት/ወያኔ ውሳኔ ተግባራዊ ማድረጉ አግባብነት የለውም እንላለን።

"አሰብ ለኢትዮጵያ ከግመል መጠጫ ሌላ ጥቅም የለውም" ተብሎ በወያኔና ሻቢያ ጥምር ተንኮል ኢትዮጵያ ተነጥቃለች። ታሪክ እራሱን ይደግማል እንዲሉ ዛሬ ደግሞ ወያኔ ከሻቢያ ጋር ላቀደው እርቅ እጅ መንሻ ይሆን ዘንድ ባድመ፣ ዛላአንበሳና ጾረና ገጸ በረከት ቀርቦላቸዋል። ይህ በኢሕአዴግ ሥራ አስፈጻሚነት ስም የተካሄደው የግዛት ቁረሳ የሀገራችንን ብሔራዊ ጥቅም የሚነካ በመሆኑ ዳግም ስህተት እየተሠራ ነው እንላለን። በታሪክም ከተጠያቂነት አያድንም እንላለን።

- የኢሕአዴግ የሥራ አስፈፃሚ ውሳኔ ላይ የተደረሰበት የሀገሪቷን ትላልቅ ተቋሞች ለሀገር ውስጥና ለውጭ ባለሀብቶች በአክሲዮን መልክ መስጠት ወቅታዊ እንዳልሆነ ልንገልጽ እንወዳለን። ቅድሚያ መሠራትና መስተካከል ያለባቸው በርካታ ጉዳዮች እያሉ ይህ እርምጃ በዘረፋና በሙስና የዳበሩ "ባለሀብቶችን" ዳግም ለዚህ አክሲዮን ግዢ ዕድል መስጠት ነው እንላለን። በሀገሪቷ ሥር የሰደደውን ቢሮክራሲና ዝርፊያ ሳያስተካክሉ ይህ ውሳኔ ሊያስከትል የሚችለውን ውድቀት ማጤን ሊዘነጋ አይገባም።

ወያኔ/ህወሓት ጠ/ሚር ዶር ዐቢይ አሕመድ እየሄዱበት ያለው አቅጣጫ የሚቀበለው አይደለም። ስለ ኢትዮጵያዊነትና ስለ ሰንደቅ ዓላማ ክብር አፉ የማይናገር፣ ጆሮው የማይሰማ፣ ዓይኑ የማያይ አገዛዝ ነውና ትልሙ ሁሉ ከዚህ አጣብቂኝ እንዴት እንደሚወጣ ነው። ህወሓት/ወያኔ መግዛት ቢያቅታቸው እንኳ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን የመበታተን አደጋ በረቀቀ መንገድ ተግባራዊ ከማድረግ አይመለሱምና ትኩረትና ጥንቃቄ የተሞላበት አካሄድ አስፈላጊነቱን እናስገነዝባለን። ከማንም በላይ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው የኢትዮጵያችን ህልውናና የሕዝባችን ደህንነት ነውና በዚህ 27 ዓመት በተደረጉ የወያኔ/ህወሓት ድራማ ሳንዘናጋ እተጀመረው ሕዝባዊ ትግል ላይ በመረባረብ ሀገራችንና ሕዝባችንን የማዳን ኃላፊነትና ግዴታ ከፊታችን መደቀኑን ልናስገነዝብ እንወዳለን።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አስተዋይነቱና ጨዋነቱን ለወያኔም ሳይቀር ይቅር ባይነቱን እያሳየ ነው የጀመረውን ትግል ጋብ ያደረገው እንጂ ተታሎ ወይም ተሞኝቶ እንዳይመስለን። አራት ነጥብ ሊደረግበት የሚገባው ጉዳይ ከእንግዲህ በምንም መልኩ ህወሓት/ኢሕአዴግ የኢትዮጵያን ሕዝብ እንዳሻው እንደማይገዛ ነው። አብቅቶለታል፣ የፍጻሜው ትግል ሕዝባዊ ድል ነው! "ጨው ለራስህ ስትል..." እንደሚባለው "አወዳደቄን ያሳምርልኝ" ብሎ የሕዝብን አስተዋይነት መቀበል ለህወሓት/ኢሕአዴግ የሚተው ምርጫ ነው። <u>ሕዝብ ግን ስቃይና ሞትን በደምና አጥንቱ ሊገላገል ቆርጦ ተነስቷል።</u>

27 ዓመት ሙሉ በውጭው ዓለም እየታገለ ያለው ፖለቲከኛ መሬት ጠብ ያለ ተግባር አላከናወነም ቢባል ያስኬዳል። ይህ ትግሉን መግፋት አለመቻሉ ለወያኔ እጅግ ተመችቶት ነበር። ሁሌም አይሆንም። ዛሬ ቢያስሩት እስር ቤት የማይበግረው፣ ቢገድሉት የማያልቅ ሕዝብ ነው የተነሳባቸው። ታጋይ የፖለቲካ ድርጅቶች ይህንን ሕዝብ ተገን አድርገው ትግላቸውን ከዳር ሀገር ወደ ሀገር ቤት ማስገባት ይጠበቅባቸዋል። ትግል ከሆነ የሚካሄደው ታጋይ ፖለቲከኞች በጋራ ተስማምተው ሀገርና ሕዝብ ለማዳን ከመቼውም በላይ ቆራጥነትና መስዋዕትነት የሚያስፈልግበት ወቅት ላይ መሆናችንን መገንዘብ ይጠበቅብናል። ለሀገርና ለሕዝብ መሞት፣ "በትግል መሞት ሕይወት" ካልን ማንኛውም መስዋዕትነት ተከፍሎ ትግሉን ለድል ማብቃት አለብን እንላለን።

ወያኔዎች የኢትዮጵያን የፖለቲካ ሥልጣን ከያዙ ጀምሮ በሀገሪቷ ሉዓላዊነትና በሕዝቧ አንድነት ላይ በተደጋጋሚ ዘምተውባቸዋል፤ አንደኛ፥ ሕዝቡን በጎሳ ለመከፋፈል ኀይላቸውን እየተጠቀሙበት ነው፤ ሁለተኛ፥ ኤርትራ ከኢትዮጵያ እንድትገነጠል የተቻላቸውን አድርገዋል፤ ሦስተኛ፥ ባድመ ለኤርትራ እንድትሰጥ በአልጀርያው ውሳኔ ተስማምተዋል፤ አራተኛ፥ የተስማሙበትን ውሳኔ በመቃወም፥ ብዙ ሕዝብ ያለቀበትን ጦርነት አካሂደዋል፥ አሁን ደግሞ ያሁሉ ሕዝብ ያለቀባትን ባድሜን ለኤርትራ እንድትሰጥ በቁጥጥራቸው ሥር ባደረጉት የኢሕአዴግ ሥራ አስፈጻሚ ስም አስወስነዋል። ይህ ደግሞ በሀገሪቷ ብሔራዊ ጥቅም ላይ ከኢትዮጵያ ሕዝብ በላይ ማንም የመወሰን መብት የለውምና ከተጠያቂነት አያድንም።

በህወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ውስጥ ብቅ ያሉት ጠ/ሚር ዐቢይ አሕመድ በቀጣይነትና ባጭር ጊዜ ወደ ተግባር በመቀየር በእንጥልጥል ያሉ የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥያቄዎች ከግብ ለማድረስ ሊወስዱቸው የሚገቡ ሁኔታዎችን እንጠቁማለን፦

- ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በውጭ ሀገርና በሀገር ቤት ለሚንቀሳቀሱ ለሁሉም ታጋይ የፖለቲካ ድርጅቶች ጥሪ በማቅረብ ሀገር አድን ጉባኤ በኢትዮጵያ እንዲካሄድ በማመቻቸት ሀገራችንና ሕዝባችን ከተደቀነባቸው አስከፊ አደጋ እናድን ዘንድ በሩን ክፍት እንዲያደርጉ እናሳስባለን።
- ማንኛውም የመገናኛ ተቋማት (ሬድዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ጋዜጣ፣ መጽሔት፣ የሶሻል ሚድያዎች፣ ወዘተ) ያለምንም ዕቀባና ተጽህኖ ይንቀሳቀሱ ዘንድ መልቀቅ፤ ለሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶችና ሌሎች አካላት አድሎ የሌለው የተመጣጠነ አገግሎት እንዲሰጡ ክፍት ማድረግ፣
- የዴሞክራሲያዊ መብቶች በተለይ የመጻፍ፣ የመናገር፣ መሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ፣ መደራጀት፣ የመሳሰሉት ያለምንም ገደብ እንዲለቀቁ፣
- በተለያዩ አካባቢዎች ለአብነት ያህል በጉጂና ጌዴዎ፣ በወላይታና ሲዳማ፣ በሱማሌና ኦሮሞ የሚካሄዱ ፍጅቶችና ማፈናቀል በአስቸኳይ ይቆም ዘንድ መመሪያ መስጠትና ተግባራዊነቱን መከታተል
- በ27 ዓመታት የህወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ያለማቋረጥ በተለያዩ የሀገሪቷ አካባቢ በየጊዜው እየተጨፈጨፈና እየተፈናቀለ ያለው የአማራ ህብረተስብ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። በአሁኑም ወቅት በጎንደር፣ ጎጃም እና በሌሎች የአማራ አካባቢዎች የሚካሄዱት አፈናና ግድያዎችን ጨምሮ የሚካሄደው የወያኔ ዘር ማጥፋት ተልዕኮ በአስቸኳይ መቆም እንዳለበት ልናስገነዝብ እንወዳለን።
- በመጨረሻም የህወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ያበቃለት ዘንድ የሽግግር መንግሥት ተመስርቶ ትክክለኛና ነፃ ሕዝባዊ ምርጫ ተግባራዊ እንዲሆን ማመቻቸት

በአሁኑ የሀገራችን ወቅታዊ ሁኔታ ከላይ የተቀመጡት ሁኔታዎች ተግባራዊ ከተደረጉ፤ የጠ/ሚሩ ጥረትና ጥንካሬ በምንፈልገው ጠንካራ ዲሞክራቲክ ህብረተሰብ፣ ጠንካራ ተፎካካሪ ፓርቲና ጠንካራ ነፃ ሚድያ ግንባታ ወደ ሥር ነቀል ለውጥ ልናመራ እንችላለን። ጠ/ሚሩ ለትክክለኛ የሥርዓት ለውጥ ያላቸውን ጥረት አመላካች ብቻ ሳይሆን በጠንካራ መሠረት ላይ የተገነባ ለውጥ እውን ይሆናል፤ በሕዝብ ዘንድ ያላቸውን ድጋፍም ይበልጥ ያጠናክረዋል እንላለን።

በማያያዝ በሀገራችን ለውጥ መጥቷል በሚል አንዳንድ ታጋይ የፖለቲካ ኃይሎች በተናጠል የሚወስዱት እርምጃ ወያኔን ከመጥቀም ባሻገር ጠቀሜታ እንደማይኖረው መናገር ይቻላል። ሕዝባችንም ደስ የሚለው፣ ህወሓት/ኢሕአዴግም እንዳበቃለት ቁርጡን የሚያውቀው ሁሉም የፖለቲካ

ድርጅቶች በጋራ አቋም ወስደው ትግሉን ሀገር ቤት በማድረግ ከሕዝባችን ጋር ለመስዋዕትነት ዝግጁ መሆናችንን ካሳየን ነው። በጠ/ሚሩም በኩል ለፖለቲካ ድርጅቶች የሚደረግ ጥሪ በተናጥል ሳይሆን ሁሉንም ሊያካትት ይገባዋል እንላለን። ስለሆነም የጠ/ሚር ዐቢይ አሕመድ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለታጋይ ድርጅቶች ጥሪ ከአቀረቡ ለያዝነው ዓላማ ፍጹምነት ካለን ለወያኔ እጅ መስጠት አይደለምና ፖለቲካ ድርጅቶችም ሊያስቡበት ይገባል። 27 ዓመት ሙሉ ፈቀቅ ያላለ ትግል የተካሄደው ፈረሱና ሜዳው ስላልተገናኙ ነውና በአራቱም ማዕዘን እየተሰዋ ያለውን ሕዝባችንን አለንልህ ካልነው ተቀላቅለነው ትግሉን ዳር ማድረስ ይኖርብናል ስንል ድምጻችንን እናሰማለን።

ስንጀምር ያስቀመጥነውን የሥርዓት ለውጥ በህወሓት/ኢሕአዴግ ሥልጣን ተጋሪነት ይመጣልናል ብለን አንጠብቅ። ሆኖም በጠ/ሚሩ የተጀመረውን ጥገናዊ አካሄድ ሕዝባዊ በማድረግ ሁሉም ሊቀየር የሚፈለገው ሥርዓት ላይ እንዲያነጣጥር ዕድሉን ልንጠቀምበት ይገባል፤ እንችላለንም። ይህ እራሱ የትግሉና የቆራጥነት አንዱ ምዕራፍ ነው።

ጥንት እንደምናውቀው ለትግል ወደ ሀገር ሲገባ እንጂ ከሀገር ሲወጣ አይደለም። ዛሬ ሕዝቡ በትግሉም ሆነ በቆራጥነቱ ቀድሞን ሂዷል። ሕዝባችን ስለ ወያኔ/ህወሓት/ኢሕአዴግ ማንነት 27 ዓመት የሕይወት ትምህርት ቤት ቀስሟልና ከታጋይ የፖለቲካ ድርጅቶች የሚጠብቀው የጋራ ስምምነት ላይ ተደርሶ ሕዝባዊ ትግሉን በመምራት ለድል ማብቃት ነው።

*"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"* ያለፉትን 75 ቀናት በጠ/ሚር ዶር ዐቢይ የሚመራው የኢሕአዴግ/ህወሓት አካሄድን ከመረመርንና ከገመገምን በኋላ የተጀመረውን ሕዝባዊ ትግል ከግብ ለማድረስ በቆራጥነት ከሕዝባችን ጎን መሰለፍ ይኖርብናል እንላለን። በዚህም መሠረት በአለፈው ከFebruary 16-19, 2018 በSeattle, Washington USA በተካሄደው የተለያዩ ፖለቲካ ድርጅቶች ጉባኤ በተላለፈው ውሳኔ መሠረት ለዚህ ኃላፊነቱን ወስዶ ትግሉን ከሕዝብ ጎን ተሰልፈን ሀገር ቤት ሜዳ የሚሆንበትን በማመቻቸት አፋጣኝ እርምጃ ይወሰድ ዘንድ እናስገነዝባለን። በተናጠል ከሚደረግ ጉዞ በጋራና በኅብረት መጓዙ ይመረጣልና በኢትዮጵያ የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት ላይና የሕዝቧ አንድነት ላይ ጥያቄ ውስጥ ከማይገቡ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር የተጀመረው የጋራ ትብብር ቀጥሎ ዋናው የተበላሸው ሥርዓት ቁንጮ ህወሓት/ወያኔ ላይ ያነጣጠረ ትግል መጠናከር ይኖርበታል ስንል አቋማችንን ግልጽ እናደርጋለን።

ለኢትዮጵያ የግዛት ሉዓላዊነት ዘብ እንቆማለን!
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!
እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!
አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ
ሰኔ 14 ቀን 2010 ዓ.ም. (June 21, 2018)

**ማሳሰቢያ ፡**

- ውድ ወገኖቻችን ይህንን "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" «***ኢትዮጵያችን***» ዕትም በተለይ በሀገር ቤት ኮምፒዩተር የማግኘት ዕድል ለሌላቸው በማባዛት ታሰራጩት ዘንድ ቀና ትብብራችሁን በትህትና እንጠይቃለን።
- "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. እራሱን ይፋ ያደረገ ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን የንቅናቄውን ማንፌስቶና ፕሮግራም www.ethiopiachen.org ከሚለው ድረ ገጻችን ማግኘት ትችላላችሁ።

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
info@ethiopiachen.org
ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org
www.ethiopiachen.com
ምሥለ ገጽ ፡ 1H1H Ethiopiachin